ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band


ሐምሌ 5 ቀን 2006 ዓ.ም.

**ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን መያዙን አመነ**

**የተለያዩ የፓሊቲካ ድርጅት አመራር አባላት ታሰሩ፤**

ባለፈው ማክሰኞ ሐምሌ 1 ቀን 2006 ወያኔ የግንቦት ሰባት ዋና ጸሐፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን ከየመን ደህንነቶች ጋር በመተባበር ከየመን ወደ አዲስ አበባ አምጥቶ በቁጥጥር ስር ማዋሉን በይፋ ገልጿል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በሀገር ውስጥ ህጋዊ ናቸው ተብለው በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላት ከግንቦት ሰባት እና ከኢሳት ቴሌቪዥን ጋር ተባባሪ ናችሁ በሚል ከያሉበት ታፍሰው ለእስር የተዳረጉ መሆናቸው ታውቆዋል፡፡

ከተለመደው የወያኔ ፕሮፓጋንዳ በተጨማሪ “ ይህ ለእኔ ጥሩ አጋጣሚ ነው፤ እረፍት ብቻ እፈልጋለሁ በጣም ደክሞኛል ልቤ ውስጥ ምንም ዓይነት ጥላቻ የለም” ወዘተ.. የሚሉ ቃሎች ከአቶ አንዳርጋቸው ሲነገሩ ተደምጧል። ሰሞኑን በርካታ ወጣት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በቁጥጥር ስር እየዋሉ ሲሆን ፡፡ የሌላ ሀገር ዜግነት ያላቸው... የህጋዊ ፖለቲካ አባልነትን እና ጋዜጠኝነትን የመሳሰሉትን ሽፋን በመጠቀም በሽብር ተግባር ላይ በመሳተፍ ላይ ነበሩ የተባሉን በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ስር ያዋለ መሆኑን ወያኔ በይፋ ገልጾዋል፡፡ ከተያዙት መካከል የአንድነት ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ሀብታሙ አያሌው እና የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ምክትል ኃላፊ አቶ ዳንኤል ሽበሺ ማክሰኞ ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር አቶ አብርሀ ደስታ ረቡዕ ሐምሌ 2 ቀን 2006 ዓ.ም ደግሞ በቁጥጥር ስር መዋላቸው ታውቆዋል፡፡ አቶ ሀብታሙ አያሌው በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት በተለምዶ ጨርቆስ ተብሎ በሚጠራው የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ በአቢሲኒያ ባንክ ውስጥ ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ እንደሆነም ታውቆዋል፡፡

ፓርቲው ደጋፊዎቹን ለማነጋገር እና ገንዘብ ለማሰባሰብ ይረዳው ዘንድ ሁለት ልዑካን ቡድን ወደ አሜሪካ እንዲጉዋዙ ካዘጋጃቸው መሀከል በአንደኛው ቡድን ውስጥ አቶ ሀብታሙ የሚገኙበት ሲሆን ለጉዞዋቸው አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ሲያደርጉ በነበሩበት ወቅት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን አባሎች ድንገት በፓትሮል አፍነው ወደ ማዕከላዊ ምርመራ እንደወሰዱዋቸው ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

አቶ ሀብታሙም ሆኑ ሌሎቹ እስረኞች በአሁኑ ሰዓት በማዕከላዊ ምርመራ እንደሚገኙና ቃላቸውን ሰጥተው እስኪያበቁ ድረስ ከማንም ጋር መገናኘት እንደማይችሉ በፖሊስ እንደተገለጸላቸው ለቤተሰቦቻቸው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልጸዋል፡፡

የአንድነት ፓርቲ የድርጅት ጉዳይ ምክትል ኃላፊ አቶ ዳንኤል ሽበሺም በበኩላቸው ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ረፋዱ ላይ በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን እጃቸው ከተያዘበት ሰዓት ጀምሮ በበርካታ

የፌዴራል ፖሊሶች እና ሲቪል በለበሱ የደህንነት ሰዎች ተከብበው መኖሪያ ቤታቸው ሲፈተሽ እንደነበርም ታውቆዋል፡፡

የሰማያዊ ፓርቲ የብሔራዊ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ አቶ የሺዋስ አሰፋ በተመሳሳይ ሁኔታ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ድንገት ከተያዙ በሁዋላ ለ24 ሰዓታት ያለ ማቋዋረጥ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ የፌዴራል ፖሊሶች እና ደህንነቶች ጭምር በተገኙበት ቤታቸው ጥብቅ ፍተሻ ሲደረግባቸው እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል።

ታፍነው የታሰሩት የተለያዩ ፓርቲዎች አመራር አባላትም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ሐሙስ ዕለት ሐምሌ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ተብሎ ቢጠበቅም ወያኔ ያላቀረባቸው ሲሆን የህግ ባለሙያዎችም እንዳያገኙዋቸው የተደረገ መሆኑ ታውቋል። ባሁኑ ወቅት በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ማወቅ ያልተቻለ ሲሆን ምናልባትም ድብደባዎች ሳያካሂዱባቸው እንዳልቀረ ይታመናል።

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህርና የአረና ፓርቲ ስራ አስፈጻሚና የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የነበሩት አብርሀ ደስታም እንደ ሌሎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ሁሉ በወያኔ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት ቡድን ከመንገድ ላይ መያዛቸው ታውቆዋል፡፡

ሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም በመቀሌ ከተማ ቀበሌ 16 ተብሎ በሚጠራው ታክሲ ተራ ላይ ድንገት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቡድኑ አፍኖ የወሰዳቸው ሲሆን ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ዕለት ድረስ የት እንደታሰሩ ቤተሰቦቻቸው ጭምር እንዳላወቁም ተነግሮዋል፡፡

እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ የአረና ፓርቲ አመራር እና የመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ አቶ አብርሀ ደስታ ተይዘው ወዳልታወቀ ስፍራ ተወሰዱ ተብሎ የነበረ ቢሆንም በመቀሌ ከተማ አቅራቢያ ባዶ ስድስት ተብሎ በሚጠራው ዜጎችን የማሰቃያ እስር ቤት ሳይከቱዋቸው እንዳልቀረም ተናግረዋል፡፡

በተያያዘ ዜና ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን መረከቡን ኃይለማርያም ደሳለኝ አዲስ አበባ ለሚገኙት ለእንግሊዝ መንግስት የዓለም አቀፍ ልማትና ትብብር ሚኒስትርዋ የገለጸ መሆኑ ታወቋል፡፡

## የአባዱላ ገመዳን ሀብት ሲቆጣጠርለት የነበረው ወጣት ድንገት መሞቱ ታወቀ፤

በሌላ ዜና በመላ ኦሮሚያ ተቀስቅሶ የነበረውን የህዝባዊ አመጽ ለማረጋጋት ከፍተኛ ሚና ሲጫወት ነበር የተባለውና ከቅርብ ግዜ ወዲህ በእነ በረከት ጥርስ የተነከሰበት የኦህዴዱ ከፍተኛ ባለስልጣን አባዱላ ገመዳ ከበረሀ ጀምሮ አብሮ የኖረው ልጁ ድንገት መሞቱ ታወቀ፡፡

አባዱላ ከወያኔ ጋር ከማይጨው ጀምሮ ያመጣው እና እንደ በህር ልጁ የሚያየው ወጣት እስከ ዕለተ ሞቱ ቀን ድረስ ቤቱን ሲያስተዳድርለት እና ሲቆጣጠርለት የነበረ መሆኑም ታውቆዋል፡፡ ከዚህ ዓለም የተሰናበተው የአባዱላ ልጅ ዓርብ ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ.ም የቀብሩ ስነስርዓት የተከናወነ ሲሆን በቀብሩም ላይ አንድም ባለስልጣን እንዳልተገኘ ታውቆዋል፡፡አባዱላ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ከክልሉ ባለሀብቶች እና ከባለስልጣናቱ ጋር

የሚያደርጋቸውን የህብት ዘረፋ የሚፈጽመውና ጉዳዮችን ሁሉ የሚያጠናቅቀው እንዲሁም በተለያዩ ባንኮች የሚገቡ ገንዘቦችንም የሚቆጣጠርለት የኸው የወጣት የነበረ መሆኑ ተነግሯል።

በኦሮሚያ የተከሰተውን ብጥብጥ ተከትሎ ለማረጋጋት በስፍራው የተገኘው አባዱላ ገመዳ የተማሪዎቹ ጥያቄ የሙብት ጥያቄ ነው ...ጥያቄውን አግባብ በሆነ መንገድ ያነሱ ቢሆንም በጸጥታ ኃይሉ የተወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ጉዳዩ እንዲጣራ እናደረጋለን በማለት በመናገሩ የተበሳጩና የተቆጡት የበረሀ ከፍተኛ ባለስልጣናቱ ጥርስ ነክሰው ሲያፈጡበት ከጎኑ ሆኖ ሲያበረታታው የነበረው ይኸው ልጅ መሆኑ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በኦሮሚያ ተከስቶ የነበረው ብጥብጥ የኦህዴድ ካድሬዎች እጅ አለበት ለማስባልና ምንጠራ ለማካሄድ የባዴንና የወያኔ ባለስልጣናት ያደረጉት ሽረባ ባለመሳካቱ አባዱላ ባደራጃቸው የኦህዴድ ካድሬዎች በተሸረበ ሴራ ነው ተግባራዊ ያልሆነው በሚልም እየወነጀሉት መሆኑ ታውቆዋል፡

በግምገማ ተወጥረው የሰነበቱት የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ያደረጉት የእርስ በርስ ግምገማ ውጤታማ ካለመሆኑም በተጨማሪ የበረሀ ባለስልጣናቱ እንደፈለጉት ባለመሆኑ በመበሳጨታቸው ካድሬዎቹን ከኦነግ ጋር በማያያዝ የምንጠራ ዘመቻ ለመጀመር የሚያስችል ምስጢራዊ እቅድ መኖሩ ታውቆዋል፡፡